እመቤቴ በአንድ ቀን ጥምቀት ብርሃኔን መለሰችልኝ

ዓይኗ የበራላት ታዳጊ ዓይናለም ብርሃኑ

ወለተ ማርያም በዓለም ስሟ ዓይናለም ብርሃኑ ትባላለች፡፡ በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ቄራ በተባለ አካባቢ የተወለደች የአስር ዓመት ታዳጊ ነች፡፡ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአራተኛ ክፍል ትምህርቷን እየተከታተለች የምትገኘው ወለተ ማርያም የ 2001 ዓ.ም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል /ገና/ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ነው ያሳለፈችው፡፡ በማይታወቅ ሁኔታ ድንገት ሁለቱም ዓይኖቿ ማየት ተሳናቸው፡፡

በሁኔታው የተደናገጡትና ግራ የተጋቡት ቤተሰቦቿ ውለው ሳያድሩ በአዲስ አበባ ውስጥ አሉ ከሚባሉ የዓይን እስፔሻሊስት ሀኪሞች ዘንድ ወሰዷት፡፡ ገንዘባቸውን ጨረሱ እንጂ መፍትሔ ግን አላገኙም ነበር፡፡ የዓይናለም ቤተሰቦች ዙሪያው ገደል በሆነባቸውና ግራ በተጋቡበት ወቅት ግን የእመቤታችን አማላጅነት ከጭንቀት ታደጋቸው፡፡

እምቦቃቅላዋ ወለተ ማርያምም በጣፈጠ አንደበቷ ስለተደረገላት ድንቅ ሥራ እንዲህ በማለት ነበር የገለጸችው «ቤተሰቦቼ በተፈጠረብኝ ነገር በጣም ተረብሸው ነበር፡፡ እኔም ዓይኔ ጠፍቶ እንዴት እንደምሆን ተጨንቄና አዝኜ ነበር፡፡ ሌትም ቀንም አለቅስ ነበር፡፡

በሐኪም መፍትሔ ያጡት ቤተሰቦቼ የተለያዩ የጠበል ቦታዎች እየወሰዱኝ እጠመቅ ነበር፡፡ ለውጥ ግን ማምጣት አልቻልኩም፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ እያለሁ አባቴ ለታናሽ ወንድሙ ማለትም ለአጐቴ ስለእኔ ሁኔታ በጭንቀት ሲነግረው አጎቴ ባጋጠመኝ አደጋ አዝኖ ጊዜ ሳያጠፋ የአባቴ እኅት ከሆነችው አክስቴ ጋር ሆነው በታኅሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ ፃድቃኔ ማርያም ገዳም ይዘውኝ ሔዱ፡፡ በሰው እየተመራሁ ወደ ገዳሙ ምሽት ላይ ደረስን፡፡

በበነጋታው እለቱ ቅዳሜ ታኅሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተዓምረ ማርያም ሰምተን ኪዳን አድርሰን ከጨረሰን በኋላ ሁሉም ምእመን እንደሚያደርገው ወደ ጠበል ቦታ በቤተሰቦቼ

አማካኝነት ሄጄ ተጠመኩኝ። በወቅቱ ጠበሉ ገና ሰውነቴ ላይ ሲያርፍ የተሰማኝን የሰላምና የመረጋጋት ስሜት መቼም አልረሳውም። ተጠምቄ ከወጣሁ በኋላ እምነቱን ዓይኔን ተቀባብቼና ጠበሉን ጠጥቼ ወደ ማረፊያ ቦታችን ሄደን። ትንሽ አረፍ እንዳልኩ ዓይኔን በጣም አሳከከኝ የሆነ ነገር ዓይኔን ወደውጭ ሲገፋው ታወቀኝ። በቃ ዓይኔ ተጎልጉሎ የወጣ መስሎኝ ተረበሽኩ፤ አለቀስኩ። ሁኔታዬን ያስተዋለችው አክስቴ ጊዜ ሳታጠፋ ወደ ዋሻ ይዛኝ ገባች። ይሁን እንጂ ፋታ ከማግኘት ይልቅ ዓይኔን በጣም ይቆረቁረኝ ጀመረ። የሚቆረቁረኝ ነገር ምን እንደሆነ አክስቴ ዓይኔን ገልጣ ብታይልኝም ምንም ነገር አላገኘችም።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ጥቂት ደቂቃዎች ካለፉ በኋላ ድንገት ዓይኔ ለሦስት ጊዜ ብርት ጭልም እያለ በመጨረሻ ከፊት ለፊቴ የነበረውን የእመቤቴን ሥዕል በደንብ ለማየት ቻልኩኝ።»

ወዲያው እንባዬ እየፈሰሰ ለአክስቴ ዓይኔ እያየ ነው ብዬ ነገርኳት። አክስቴ የምታየው ነገር ከቁጥጥር ውጭ ስለሆነባት እያለቀሰችና እየጮኸች የእመቤታችንን ድንቅ ሥራ መናገር ጀመረች።

የተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን አይተውና ሰምተው ወዲያው በእንባ እመቤታችንን ማመስገን ጀመሩ። የጸሎት ቦታው በአንድ ጊዜ በደስታና በለቅሶ ተሞላ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአንድ ቀን ጥምቀት በእለተ ቀኗ የልጅነት ብርሃኔን መለስችልኝ አይቼ የመጣሁበትን ቦታ እንዳመሰግን አደረገችኝ። እንደገናም ፈጠረችኝ። ምስጋና ይድረሳት የእኔን ዓይን ያበራች እናት ለእናንተም መልካም የሆነውን ብርሃን ታብራላችሁ። እሷን መድኃኒት አድርጎ የሰጠን መድኃኔዓለም ክብሩ ለዘላለም ይሁን» በማለት ነበር ስለተደረገላት ድንቅ ሥራ የመሰከረችው። ሕፃኗ የአስር ዓመት ልጅ ሊናገረው ቀርቶ ሊያስበው ይከበደዋል የተባለውን ምስክርነት ስትሰጥ ለሰማት የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እያየ ይደነቃል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተቸገርንበትና መልስ ባጣንበት ነገር ሁሉ ከጐናችን ትሆን ዘንድ መልካም ፍቃዷ ይሁን አሜን።
ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ።